# ሥነ-አመክንዮና ስሜት

ሥነ-አመክንዮና (logic) ስሜት (emotion) - ለየቅል ነው እንጂ - ሁለቱም በፖለቲካ ውስጥ ሚና አላቸው። በርግጥ ብዙ ሰው በስሜት ውስጥ ይመሰጣል ምክንያቱም ሥነ-አመክንዮ በርካታ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ለመመለስ ዝግጁ አልሆነም። ፖለቲካ ግልጹን አይናገርም፣ ወድያ ወዲህ ይዋልላል። መልካም ፖለቲካ የማንስማማቸውን ነገር ነቅሶ አውጥቶ ለማግባባት መጣር ነው። ምክንያቱም የማንግባባው ምክንያታዊ ሆነን አይደለም፣ ሊያግባባን የሚችለውን ሥነ-አመክንዮ ስላልተረዳን ነው። ሁለቱም ተከራካሪ ወገን ማስረጃ ሲያጣ ወደ ግምት (opinion)ውስጥ ይገባል። ግምት ደግሞ ቤቱን ሲቆጣጠር ስሜት ታብጣለች።

ስሜት ለማምታታ ወይም ብዙሃኑን ለማንቀሳቀስ (manipulation) ዋነኛ መሳርያ ነች። ስሜት በሰው ልጅ ጠባይና ባህርይ ውስጥ የመሸገች በመሆኗ በማስታረቅ፣ ማጋጨትም ይሁን በሌሎች ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ ታላቅ አስተዋጾ ታደርጋለች። ርዕዮተ ዓለም በስሜት አይበጅም ግን አነሰም በዛም አንዱ በአንዱ ላይ ተጽዕኖ(interaction) ያሳርፋሉ። በአንድ ስብሰባ ውስጥ አብዛኛውን ለማሳመን ወይም ለማስተማር ስሜትን ማርገብ መቻልና ሳይዋሹ ሃቁን መግለጽ አዋቂነት ነው። የመጣው ይምጣ እውነቱን የሚናገር ፖለቲከኛ ጀግና ነው።

ሥነ-አመክንዮ ሠፊ ንግግር፣ ምክንያት፣ ህግ፣ ንፅፅር - ሊሆን ትችላለች። በእርግጥ እነዚህ ጽንሶች ብቻቸውን ሥነ-አመክንዮን በሚገባ ይገልጻሉ ሊባል አይችልም። ሥነ-አመክንዮ ምን ማለት እንደሆን መግለጽ ይከብዳል። ሥነ-አመክናዓ እውነት ማለት ሊሆን ይችላል። ምናልባት ሥነ-አመክንዓ "የትክክለኛ ምክንያት መርህ ጥናት ነው" ቢባል"ጽንሱን በተሻለ ለመረዳት ይጠቅም ይሆናል" ይላሉ ተመራማሪዎች። ፈላስፎች "ሥነ-አመክንዮ የምክንያት ሥነ-ልቦና ጉዳይ አይደለም" ይላሉ። ይልቁንም ሥነ-አመክንዮ ቀዳሚ ስለሆነ፣ እንዴት ምክንያት እንደምናበጅ ያስረዳናል ሲሉ ያክላሉ። "ምክንያታዊ መሆን ከእድሜ መግፋት ጋር አብሮ ይሄዳል፣ ሥነ-አመክንዮ ግን የእድሜ ገደብ የለውም" የሚል ጥናታዊ ጽሑፍም እንዳለ ይነገራል።

እስኪ የምክንያታዊነት መርህ ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት። ብዙ መርሆች አሉ፣ ቢሆንም ግን ሥነ-አመክንዮን ስናጠና ዋነኛው ክርክሩን ወይም ውይይቱን ዋጋ የሚሰጠው ጉዳይ ማጤኑ ነው። እነዚህን ምሳሌዎች እንመልከት።

ሃቀኛ የሃገር መሪ ሙስናን ይጠየፋል
እገሌ -ሃቀኛ የሃገር መሪ ናቸው
ስለዚህ፤ እገሌ ሙስናን ይጠየፋሉ።

የኃይማኖት ሰዎች ብዙ ገንዘብን አይሹም
አባ --- የኃይማኖት ሰው ናቸው
ስለዚህ፤ አባ --- ብዙ ገንዘብ አይሹም።

ሥነ-አመክንዮ የመጀመርያውን ትክክለኛ ሃሳብ ወይም ጠንካራ ግምት ይከተላሉ። የመጀመርያዎቹ ሃሳቦች ደግሞ ሁልጊዜ ትክክል መሆን አለባቸው ማለት ነው። ሃቀኛ የሃገር መሪ ሙስናን መጸየፉ ትክክል ነው። የኃይማኖት ሰዎች ብዙ ገንዘብ አለመሻታቸውም ትክክል ነው። ከዚህ ውጭ ያለው ሥነ-አመክንዮን አይከተልም።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ሥነ-አመክንዖ ለማስተማር ሳይሆን ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለምን ከሥነ-አመክንዖ ይልቅ በስሜት ይነዳሉ የሚለውን በትንሹ ለማየት ነው። ከላይ በምሳሌ እንዳየነው የሃገር መሪውን ሙስናን ስለሚጸየፉ ነው የምንወዳቸው። አባ ለሁላችን ምሳሌ የሆኑ፣ አፍቅሮ ነዋይ የማይታባቸው አባት ስለሆኑ ነው የምንከተላቸው። ሁለቱም እነዚህን ጥሩ ባህርያትን ካላዘሉ አንከተላቸውም። ሁለቱንም ከተከተልናቸው ግን በስሜት ተነድተን ወይም በጥቅም ተይዘን ነው ማለት ነው። ስሜት አይላ ሥነ-አመክንዖ ከታቀበ ወደ ትክክለኛው ግንዛቤ መጓዝ አይቻልም።

ፖለቲከኞች በምርጫ ወቅት "ይህን አደርግላችኋለሁ - ምረጡኝ" ይላሉ። ብዙ ሰዎች -ያ- ቃል የተገባለቸው ነገር የሚደረግላቸው እየመሰላቸው ተናጋሪውን እጩ ይመርጣሉ። ከዓመታ በኃላም ይኸው ይደገማል፣ ጠብ የሚል ግን የለም። ለዚህ ነው ሰዎች ከፖለቲከኞች ይልቅ ከያኔዎችን፣ አርቲስቶችንና የሡብዓዊ መብት ተሟጓቾችን የሚከተሉት። ከያኔው፣ አርቲስቱና የሠብዓዊ መብት ተሟጋቹ - ቢያንስ ቢያንስ – ፖለቲካውን ስለሚያብጠለጥሉትና ፖለቲከኛውን አደብ ስለሚያሲዙት የብዙ ሰዎችን ስሜት ይማርካሉ።

ስሜት ግን ለፖለቲካ ድርጅቶች ቁመና መልካም አይደለችም። በተለይ ደሃ አገሮች በስሜት ብቻ ከተነዱ ትልቅ ተቋም (institution) መመስረት የማይችሉበት ደረጃ ደረሰው ሁልጊዜ በስሜት ብቻ ይዋጣሉ። አሁንም ጠብ የሚል ነገር አይመጣም፣ ችግሩ ይባባሳል እንጂ። ግለሰቦች መድረኩን በግላቸው ሲቆጣጠሩት ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገው ሂደት ይዘገያል። ጭብጨባ ሲበዛ እውቀት ትደበቃለች፣ ሥነ-አመክንዖም ግራ ይገባታል።

ሰዎች ብቻ አይደሉም ከያኔውን፣ አርቲስቱንና የሰብዓዊ ተሚጋቹን የሚከተሉት። ለምሳሌ አንድ ቱጃር በሕዝብ እንዲወደድ ከፈለገ በሕዝብ የሚወደደውን ዘፋኝ ይደግፈዋል፣ በችግሩ ጊዜ ይደርስለታል። ይኸው ከበርቴ አንድ ብዙ ተከታይ ያለውን አርቲስት በእጁ ካደረገ ማንም ተነስቶ በንግግር አይሸነቁጠውም፣ አይቃወመውም፣ ንግዱም ኪሳራ አይደርስበትም። ከበርቴው ግን ወርቅና ማዕድን የሚያሸሽ፣ አምባገነኖችን በሙስና የሚያባልግ፣ ደሃን ቁልቁል የሚጫን ጨካን ነጋዴ ሊሆን ይችላል። ስሜት ጥቅምን ልታስቀድም ትችላለች። ስሜት ፍቅር ላይታያት ይችላል። ብልጣብልጦች ደግሞ ስሜትን እንደየፍጆታው ይጠቀሙባታል። የፖለቲካ መሪዎች፣ የሃገር መሪዎች፣ ከበርቴዎችና ታዋቂ ሰዎች - ከያኔዎችን፣ አርቲስቶችንና የሡብዓዊ መብት ተሚጋቾችን የሚይዙት ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ነው።

ችግሩ ከያኔዎች፣ አርቲስቶችና የሠብዓዊ መብት ተሚጋቾች ተቋም (institution) አለመሆናቸው ነው። ጠንካራ ተቋም በሥነ-አመክንዖ የሚመራ የፖለቲካ ፓርቲ ነው። ይህ የፖለቲካ ፓርቲ ትክክለኛ መርህን በመምረጥ ምክንያታዊ ለመሆን ዘወትር መጣርና መማር አለበት። አሁን ላይ ጠንካራ ፓርቲ ሊኖር የቻለ አይመስልም። ምክንያቱን ኢህአዴግ ጠንካራ ፓርቲ እንዳይኖር ብዙ ኃይሉን ተጠቅሟል። ኢሕአዴግ ታጋዮችን አጥፍቷል። ጥቂት የቀሩት ጀግኖችም ክብር ይገባቸዋል። ዶክተር አብይ በሃሳብ የሚበልጠውን ፓርቲ "ተፎካካሪ ፓርቲ" ብለውታል። ሃሳብ ከሌለው ግን ሥራው በስሜት መቃወም ብቻ ይሆናል። ሃሳብ ደግሞ በእውቀትና ምርምር እንጂ በስሜት አትገኝም።

ጠንካራ ፓርቲ እንዲኖር ስሜት ጋብ ማለት አለባት። ጠንካራ ፓርቲ እንዲኖር ሥነ-አመክንዖ ማደግ አለበት። የፖለቲካ ፓርቲ በአዋቂዎች፣ ምሁራንና ጉጉት በማይበረታበቸው ሰዎች ሲመራና ሃሳብ መሬት ስትወርድ ሃገር ከድህነትና እርዛት በቶሎ ትላቀቃለች። የዛሬው የሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ለዚህ ጉዳይ ምቹ ይመስላል። ከያኔዎችና አርቲስቶችና መላው የኪነ ጥበብ ሰዎች በሙያቸው ምክንያታዊነትን የሚያግዙ ሥራዎችን ሲከውኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችና አባላቶቻቸው በእውቀትና ጥበብ

ይመነደጋሉ። ኪነ ጥበብ ሕዝቡ እንዲደራጅና እንዲማር ቅስቀሳ ማድረግ ይጠበቅባታል። ይህን ጊዜ የስሜት ቴርሚሜትር ሲያሽቆለቁል የሥነ-አመክንዮው ደግሞ ወደ ላይ ከፍ ይላል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር